https://chilot.me


# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምተኛ ዓመት ቁጥር ፹፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 86
ADDIS ABABA August 15th, 2019


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፬/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የማዕድን ግብይት አዋጅ........................ገጽ ፲፩ሺ፮፻፵፩


CONTENT


Proclamation No.1144/2019

Transaction of Minerals Ratification Proclamation.......................................Page 11641


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፬/፪ሺ፲፩

## የማዕድን ግብይትን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ድንጋጌ መሰረት የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት መንግስትና ሕዝብ በመሆኑ፤ የማዕድን ሀብትም ከተመረተ በኋላ ያለውን የግብይትሥርዓት በሕግ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሁሉንም ዓይነት ማዕድን ግብይት ለማስፋፋት፣ ሕጋዊ ሥርዓት ለማስያዝና ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ ሆኖ በመገኘቱ፤

የማዕድን ግብይት ሥርዓትን ዘመናዊ በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ለማሳደግ የሚያስችል የግብይት ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

## PROCLAMATION NO. 1144/2019

## A PROCLAMATION TO REGULATE TRANSACTION OF MINERALS

**WHEREAS**, the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, provides that the Right to Ownership of all-natural resources of Ethiopia is exclusively vested in the Government and its People. Thus, it becomes necessary to regulate the transaction of mineral resources after production;

**WHEREAS**, it has become necessary to put in place a regulatory framework that promote, regulate and control the transaction of all mineral resources;

**WHEREAS**, it has become necessary to modernize the mineral transaction scheme so as to create a proper structure that enhances the contribution of the sector to the National Economy;

https://chilot.me



በማዕድን ግብይቱ ላይ የሚሳተፉ አካላት ሚና ሥልጣንና ተግባር መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የማዕድን ግብይት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፬/፪ሺ፲፩ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውኃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተራፊ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም ከቀሪ የማዕድን ክምችት ውስጥ የተመረተ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

ሀ/ ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ጨዋማ ውኃ በስተቀር፤ ለኢንዱስትሪ፣ ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ እና ለሕክምና የሚውል የጂኦተርማል ውኃ እና ሌላውን ውኃ፣

ለ/ አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይት እና ጋዝ፣

ሐ/ ከነዳጅ አዘል አለት የተመረቱ ውጤቶችን፤

፪. "የከበረ ማዕድን" ማለት እንደ ፕላቲንየም፣ ወርቅና ብር የመሰለ የከበረ ብረት ነክ ማዕድን ወይም እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኤመራልድ፣ ሳፋየር ያለ ከከበረ ድንጋይ የተመረተ ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

**WHEREAS**, it has become crucial to determine the roles, Powers and Duties of all stakeholders that participate in mineral transaction;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**PART ONE**

**GENERAL**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Transaction of Minerals Proclamation No. 1144 /2019."

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1. "Mineral" means any mineral substance of economic value produced, whether in solid, liquid or gaseous form, occurring naturally on or within the earth or in or under water and which is formed by or subjected to geological process and includes any mineral occurring in residue stockpiles or in residue deposits but excludes:

   a. Any other water and Geothermal water used for industrial, bathing, recreational and medical purpose other than water used for the extraction of any mineral such as brine;

   b) Products of Natural gas and Petroleum as defined in the relevant petroleum law;

   c) Top soil and products of oil shale;

2. "Precious Mineral" means precious metallic mineral such as platinum, gold, silver or precious stones such as diamond, ruby, emerald, sapphires products and includes other minerals as the ministry may, by Directives, so designate;

https://chilot.me



፫. "በከፊል የከበረ ማዕድን" ማለት ለማስዋቢያነት የሚውል ወጥ ወይም በተፈጥሯዊ አንድነት የተጣመረ እንደ ሮዶላይት፣ ኦሊቪን፣ ኦፓል፣ ጃዲያትና ላዙራይት የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩ ማድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ በከፊል የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፬. "ብረት ነክ ማዕድን" ማለት እንደ ብረት፣ መዳብ፣ ነሐስ፣ እርሳስ፣ ክሮማይት፣ ኒኬል፣ ታንታለም እና ማንጋኒስ የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ ብረት ነክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፭. "የግንባታ ማዕድናት" ማለት ማናቸውም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኮንስትራክሽን በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ዕብነበረድ፣ ግራናይት፣ ላይምስቶን፣ ባዛልት፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ኢግኒምብራይትና የሸክላ አፈር የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ሌላ ማዕድንን ይጨምራል፤

፮. "የኢንዱስትሪ ማዕድን" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ኳርትዝ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ላይምስቶን፣ ፖታሽ፣ ጂፕሰም፣ ፑሚስ፣ የሸክላ አፈርና ግራፋይት የመሰለ ማንኛውም ማዕድን ሲሆን፣ ብረት ነክና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ የኢንዱስትሪ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፯. "ግብይት" ማለት ማዕድናትን ለንግድ ዓላማ ለመግዛት፣ ለመያዝ፣ ለማጓጓዝ፣ በዕደ ጥበብ ሙያ ለማዘጋጀት፣ ለማጣራት፣ ለማቅለጥ፣ በሀገር ውስጥ ለመሸጥ ወይም ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፡፡

3. "Semi-Precious Mineral" means mineral used for jewelers such as opal, rhodolite, olivine, jadite, lazurite and includes any other mineral the Ministry may, by Directives designate as such, excluding precious minerals;

4. "Metallic Mineral" means any produced metallic mineral such as iron, copper, zinc, lid, chromites, nickel, tantalum and manganese and includes any other mineral the ministry may, by directives, designate as such, excluding precious and semi-precious minerals;

5. "Construction Mineral" means any mineral directly or indirectly used as an input for construction purposes such as marble, granite, limestone, basalt, sand, aggregate, ignimbrite, and clay and includes any other non metallic minerals the ministry may designated as such by Directives;

6. "Industrial Mineral" means any mineral directly or indirectly used as industrial input such as kaolin, bentonite, quartz, coal, limestone, potash, gypsum, pumice, clay, graphite and includes any other minerals the ministry may, by directives, designate as such, excluding metallic, precious or semi-precious minerals;

7. "Transaction" means any activity related to the purchase, custody, transport, crafting, refining, smelting, sale locally or export of minerals for commercial purposes;

https://chilot.me



፰."አቅራቢነት" ማለት በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወርቅና ብር ማዕድናትን ከሕጋዊ አምራች በመግዛት ለብሔራዊ ባንክ አካል፤ ከወርቅና ብር ውጪ ያሉ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ለላኪዎች ወይም የመቅረጽ የዕደ ጥበብ ፈቃድ ላላቸው እና ከነዚህ ከተጠቀሱት ውጪ ያሉትን ማዕድናት ለተጠቃሚዎች የመሸጥ ሥራ ነው፤

፱. "ዕደ ጥበብ" ማለት ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ ወይም ከብረት ነክ ማዕድናት በማንጠር ወይም በመቅረጽ ወይም የሁለቱን ውጤት አጣምሮ ሌላ ቅርጽ በማስያዝ ማዕድናት የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዲይዙ የማድረግ ሥራ ነው፤

፲. "ማንጠር" ማለት የከበሩ ብረት ነክ ማዕድናትን ለተጠቃሚ ፍጆታ በሚሆን መልኩ ማቅለጥ፣ ቅርጽ ማውጣትና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን ነው፤

፲፩. "መቅረጽ" ማለት የከበሩና በከፊል የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናትን የመጨረሻቸውን ቅርጽ እንዲይዙ ለማድረግ የሚከናወን የመቁረጥ፣ ቅርጽ የማውጣት፣ የማለስለስና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ማከናወን ነው፤

፲፪ "ማጣመር" ማለት በማንጠር ወይም በመቅረጽ ሥራ የተሰራ ያለቀለት ወይም በከፊል ያለቀለት ጌጥ በመጠቀም የሁለቱ ጥምረትና ውጤት የሆነ የመጨረሻ ቅርጽ ያለው ጌጥ የማምረት ሥራ ነው፤

፲፫. "ማቅለጥ" ማለት ወርቅ፣ ብር ወይም ብረት ነክ ማዕድናትን ለሽያጭ ሊቀርቡ በሚችሉ መልኩ አቅልጦ የተፈለገውን ቅርጽ የማስያዝ ሥራ ነው፤

፲፬ ."ማጣራት" ማለት የብረት ነክ ማዕድናትን ጥራት ለመጨመር ከውስጣቸው ያለውን አላስፈላጊ ንጥረ ነገር ማስወገድ ወይም አብረው ያሉ ተያያዥ ማዕድናትን ለመለየት የሚከናወን ተግባር ነው፤

8. "Suppliers" means a buyer of locally produced minerals from legal miners and sale gold and silver to national bank precious or semi-precious minerals to exporters or holders of lapidary license and the remaining minerals to the users;

9. "Crafting" means the activity of molding precious, semi-precious or metallic minerals in their final shape by means of smithery, lapidary or by combining the output from the two;

10. "Smithering" means undertaking smelting, molding and other similar activities of precious, semi-precious or metallic minerals to finished products for consumption by end users;

11. "Lapidary" means the cutting, molding, polishing and any other similar activities carried out on precious and semi-precious stone to shape them to be ready for use;

12. "Combining" means using processed or semi processed ornament to produce a combined ornament that has final shape by means of smithery or lapidary;

13. "Smelting" means the process of giving final shape to gold, silver or metallic minerals through smelting and make them ready for sale;

14. "Refining" means the process of taking out of impurities or separation of different associated metals from any metallic minerals to increase their carat amount or purity;

https://chilot.me



፲፭. "ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም የማዕድናት ግብይት ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ነው፤

፲፮. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆኑ የሚሰጥ ሠነድ ነው፤

፲፯ "ማሰናዳት" ማለት ማዕድናት የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዲይዙ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማጠብ፣ ማቅለጥ፣ ማንጠር፣ መፍጨት፣ መቁረጥ፣ ቅርጽ ማውጣት፣ ማስዋብ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን ማከናወን ነው፤

፲፰. "የውጭ ባለሀብት" ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ ዜጋ ወይም በውጭ ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ሲሆን እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ ሀገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል፤

፲፱. "የሀገር ውስጥ ባለሀብት" ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መንግሥትንና የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደ ሀገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ሀገር ዜጋን ይጨምራል፤

፳. "ላኪነት" ማለት ወርቅና ብር ሲሆን የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ፣ ሌሎች ማዕድናት ሲሆን በጥሬ ወይም በከፊል የተሰናዳውን ከአምራች፣ ከዕደ ጥበብ ወይም ከአቅራቢነት ባለፈቃድ በመግዛት ወደ ውጭ ሀገር የመላክ ሥራ ነው፤

፳፩. "ማስተላለፍ" ማለት መሸጥ፣ በዕዳ ማስያዝ፣ ማውረስ፣ መዳረግ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ አንድ ሰው ያለውን መብትና ግዴታ የሌላ ሰው እንዲሆን ማድረግ ነው፤

15. "License" means a trade license issued pursuant to the provisions of this proclamation that gives a mineral transaction right;

16. "Certificate of Competence'' means a certificate granted to approve the capability of an applicant to get a trade license to engage in minerals transaction;

17. "Processing" means washing, smelting, smithering, crushing, cutting, decorating minerals by using different methods and undertaking other related activities to give their final shape;

18. "Foreign Investors" means Foreign National or an enterprise owned by foreign nationals, having invested foreign capital in Ethiopia, and includes an Ethiopian permanently residing abroad preferring treatment as a foreign investor;

19. "Local Investors" means an Ethiopian having made an investment, or Government and Public Enterprises as well as a Foreign National of Ethiopian origin and preferring treatment as a domestic investor;

20. "Exporting" means the activity of buying gold and silver which are in their final shape, other mineral in their processed or semi processed form, from miners, holder of crafting or suppliers license for the purpose of exporting;

21. "Transfer" means sale, encumbrance, inheritance, assignment or any other means of transferring of the Rights and Obligations to another party;

፳፪. "ተረፈ ምርት" ማለት ማዕድናት ሲሰናዱ የሚገኙ ስብርባሪ፣ ውዳቂ፣ አሰር፣ ዝቃጭ፣ ቆሻሻ አዘል ድፍርስ፣ ቆሻሻ፣ አመድ የመሳሰሉት ሲሆኑ ዋጋ ያላቸውና ዋጋ የሌላቸውን እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ወይም ጉዳት የማያደርሱትን ያካትታል፤

፳፫. "የግል መጠቀሚያ" ማለት ለንግድ ዓላማ ሳይሆን ግለሰብ በጌጥ መልክ የሚጠቀምበት የመጨረሻ ቅርፁን ያያዘ ወርቅና የከበረ ብረት ነክ ማዕድን፣ የከበረ የጌጥ ማዕድን ወይም በከፊል የከበረ ማዕድን ነው፤

፳፬. "ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን " ማለት እንደ አግባቡ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ነው፤

፳፭. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ ባለሥልጣን" ማለት እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የማዕድን ዘርፍ ሥራ የሚመለከተው የክልል አካል ነው፤

፳፮. "ሚኒስቴር" ማለት የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ነው፤

፳፯. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፳፰. "ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፳፱. "የፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዘመን" ማለት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር የአንድ አመት ጊዜ ነው፤

፴. "የበጀት ዓመት" ማለት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴ ቀን ያለው ጊዜ ነው፤

22. "By-products" means debris, discard, tailings, slimes, slurry, waste, ash or any other products derived from processing minerals including those that have value or no value, or that causes or may not cause harm to the environment;

23. "Personal use" means the custody of gold and precious metallic minerals, precious ornament or semi-precious mineral by individual for non-commercial purpose which is in their final shape ready for ornamental purpose;

24. "License Issuing Authority" means as the case may be the Ministry of Trade and Industry or any relevant regional authority.

25. ''Certificate of Competence Issuing Authority'' means as the case may be the Ministry or any regional authority responsible for managing the mineral sector;

26. "Ministry" means the Ministry of Mines and Petroleum;

27 . "State" means any regional state specified under article 47 (1) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

28. "Bank" means the National Bank of Ethiopia;

29. "Duration of a License or Certificate of Competence" means a duration of one year from the issuance of a license or certificate of competence, in the Ethiopian Calendar;

30. "Budget Year" means from the period of July 08 up to July 07, according to the Ethiopian calendar;

https://chilot.me



፴፩. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፪. "የመጨረሻ ቅርጽ" ማለት በማዕድናት ላይ ሴት በመጨመር ለግል ማስዋቢያ ወይም ማስጌጫ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ያለቀለት የማዕድናት ምርት ውጤት ነው፤

፴፫. ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ድሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚካሄድ በማናቸውም መንገድ በሚመረቱ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ያመረተውን ማዕድን በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ለመሸጥ በዚህ አዋጅ የተጠቀሰው ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አያስፈልገውም፡፡

## ፬. ዓላማ

የዚህ አዋጅ ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. ለሚመረተው ማዕድን ጠንካራ የግብይት ሥርዓት በመፍጠር የሀገሪቷ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ የጎላ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ፣

፪. የማዕድኑን የግብይት ሥርዓት ወቅታዊ አድርጎ በማደራጀት ግብይቱን ከሕገወጥ ተጽዕኖዎች ለመከላከል፣

፫. በማዕድን ግብይት ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች መብትና ግዴታቸውን ተረድተው በሕጉ አግባብ መመራት እንዲችሉ ለማድረግ፤

፬. የማዕድን ግብይት ሥርዐቱ የአካባቢና ማኅበራዊ ጥበቃና እንክብካቤ መረሆዎችን በዘላቂነት በጠበቀ

31. "Person" means any Natural or Juridical Person;

32. "Final Shape" means to add value to minerals to produce jewelry and ornaments to get final aesthetic value;

33. Any expression in the Masculine Gender shall also include the Feminine gender.

## 3. Scope of Application

1. This proclamation shall apply to govern all transactions of minerals produced from all mining operations conducted within the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

Notwithstanding sub-article 1 of this Article, a holder of a mining license, subject to the provisions of the Mining Operations Proclamation, shall not be required to obtain certificate of competence or any other license specified under this proclamation in order to sale locally or export the minerals produced.

## 4. Objectives

The objectives of this Proclamation are to:

1. Create an effective transaction scheme for minerals to ensure meaningful contribution to socio-economic development.

2. Organize and update the mineral transaction scheme to prevent the transaction from illegal influences.

3. Make investors, who are engaged in minerals transactions, perform their rights and obligations as per the rules and regulations.

4. Ensure that the mineral transaction scheme is implemented taking due consideration of the environmental and social protection principles in a

ሁኔታ መተግበሩን ለማረጋገጥ፣

## ክፍል ሁለት

## ስለ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

**፭. የፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት**

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሰረት የማዕድን ግብይት ፈቃድ በማዉጣት የማዕድን ግብይት ማካሄድ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛዉም የማዕድን ግብይት የንግድ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው ፍቃዱ የሚሰጠው ከብቃት ማረጋገጫ መስክር ወረቀት ሰጪ ባለስልጣን የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስር ወረቀት ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ፈቃድ ስለ መስጠት

**፮. የፈቃድ ዓይነቶች**

በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚከተሉት የማዕድን ግብይት ፈቃዶች ይሰጣሉ ፡-

፩.የማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ፣

፪. የማዕድን ዕደ ጥበብ ፈቃድ፣

፫. የማዕድን ማጣራት ፈቃድ፣

፬. የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ፣

፭. የማዕድን ንግድ ፈቃድ

፮. የማዕድን ላኪነት ፈቃድ

**፯. የማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ**

፩. የማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ በሚከተለው ሁኔታ በየማዕድን ዓይነቱ ተለይቶ ይሰጣል፡፡

ሀ/ የኮንስትራክሽን ወይም የኢንዱስትሪ ማዕድን ሲሆን ማዕድኑን ከሕጋዊ አምራች የመግዛት፣ ለሽያጭ የመያዝ፣ የማዘዋወር፣ በሀገር ውስጥ ለተጠቃሚ ወይም የላኪነት ፈቃድ ላላቸው ሰዎች የመሸጥ መብት ይሰጣል፤

sustainable manner.

## PART TWO

## LICENSE OR CERIFICATE OF COMPETENCE

**5. Requirement of License or Certificate of Competence**

1. Any person may carry out transactions of minerals upon obtaining license pursuant to this proclamation and other relevant laws. and
2. Any person requested for trade license of mineral transaction shall present certificate of competence granted by the certificate of competence issuing. Authority.

## CHAPTER ONE

## ISSUANCE OF LICENSE

**6.Types of Licenses**

The following licenses may be issued under this Proclamation and other relevant laws:

1. Mineral supplier license;
2. Mineral crafting license;
3. Mineral refining license;
4. Mineral smelting license
5. Mineral Trade license.
6. Mineral Exporting license.

**7. Issuance of Mineral Supplier License**

1. A mineral supplier license may be issued in the following conditions upon identifying the type of mineral;

a/ When it is a construction or industrial mineral materials, the supplier license grants the holder of the license the Right to purchase mineral from legal miners, hold for sale, transport and sale the mineral

፪. የማንጠር ዕደ ጥበብ ፈቃድ ወርቅ ወይም ብርን ሕግ በሚወስነው መሠረት የመግዛት፣ የመያዝ፣ የማጓጓዝ፣ የተበላሹ ወይም የተሰበሩትን የመግዛት እና የመጠገን፣ የማንጠር ሥራ የማከናወን እና ምርቱን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የመሸጥ መብት ይሰጣል፡፡ ሆኖም ይህ ባለፈቃድ ጥሬ ማዕድናት ገዝቶ ጌጣጌጥ መሥራትና መሸጥ አይችልም፡፡

፫. የመቅረጽ ዕደ ጥበብ ፈቃድ ከወርቅ፣ ከብርና ከፕላቲንየም ውጪ ያሉትን የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት የመግዛት፣ የመያዝ፣ የማጓጓዝ፣ የመቅረጽ ሥራ የማከናወን እና ምርቱን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የመሸጥ መብት ይሰጣል፤

፬. የማጣመር ዕደ ጥበብ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያለቀላቸው ማዕድናትን የመግዛት፣ የማጓጓዝ፣ የመያዝ እና በማጣመር ጌጣጌጥ ሰርቶ ምርቱን በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የመሸጥ መብት ይሰጣል፤ ሆኖም ይህ ባለፈቃድ ጥሬ ማዕድናት ገዝቶ ጌጣጌጥ መሥራትና መሸጥ አይችልም፡፡

## ፱. የማዕድን ማጣራት ፈቃድ

የማዕድን ማጣራት ፈቃድ በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ ሀገር የገቡ ወርቅ ወይም ብር ወይም ሌሎች ብረት ነክ ማዕድናትን ከማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፣ ከባንክ ወይም ሌላ ሕጋዊ ፈቃድ ካለው ሰው ተቀብሎ የማጣራት ሥራ በማከናወን መልሶ የማስረከብ ወይም የመሸጥ መብት ይሰጣል፡፡

## ፲. የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ

የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጪ የገቡ ብረት ነክ ማዕድናትን የማቅለጥና ተፈላጊውን ቅርጽ የማስያዝ ሥራ የማከናወን መብት ይሰጣል፡፡

2. Smithery license grants the holder of the license the right to purchase, hold, transport and smithering gold or silver as promulgated by the law and sale the product locally or abroad. However, the holder of this license can not purchase, make jewelries and sale raw minerals.

3. Lapidary license grants the holder of the license the right to purchase, hold, transport, perform lapidary works and sale locally or export precious and semi-precious minerals other than gold, silver and platinum.

4. Combining license grants the holder of the license the right to purchase, hold, transport, combine and make jewelry using processed or semi-processed minerals and sale its product locally or export. However, the holder of this license can not purchase, make jewelries and sale raw minerals.

## 9. Mineral Refining License

Mineral refining license grants the holder of the license the right to refine locally produced or imported gold, silver or other metallic mineral upon receiving from miners, bank or other legally authorized person and hand over or sale after refining the mineral.

## 10. Mineral Smelting License

Mineral smelting license grants the holder of the license the right to smelt and give final shape to locally produced or imported metallic minerals.

https://chilot.me





ሐ/ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ለሆነ ሰው የማዕድናት አቅራቢነት ፈቃድ አይሰጠውም፡፡ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ላለው ሰው የተሠጠ የአቅራቢነት ፈቃድ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለ ከ ፩፻፳ ቀን በኋላ በፈቃዱ ላይ ያለው መብት ቀሪ ይሆናል፡፡

## ፲፬. ስለፈቃድ ማመልከቻ

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖው ለፈቃድ የሚቀረብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

፩. ማመልከቻው ለማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ ሲሆን፡-

ሀ/ የአመልካቹ ስም፣ የሥራ አድራሻና ዜግነት፣.

ለ/ ሊሰማራበት የፈለገውን የማዕድን ዓይነት፣

ሐ/ ማዕድኑን ሊገዛበትና ሊሸጥበት ያቀደበት ሥፍራ፣

መ/ እንደማዕድኑ ዓይነት የሚወሰን ሆኖ ቋሚ የማከማቻ ቦታ እና የመሥሪያ ቦታ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ፣

ሠ/ የንግድ ዕቅዱን፣

ረ/ በንግድ ህጉ መሰረት ለንግድ ዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልግ ካፒታል መኖሩ ማረጋገጫ፣

፪. ማመልከቻው ለማዕድን ዕደ ጥበብ ፈቃድ ሲሆን፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱትን፣

ለ/ አላስፈላጊ ተረፈ ምርቶችን የሚያስወግድበት ሥርዓት፣

license for two years following such cancellation.

c/ A supplier license shall not be issued to holder of mining license. The rights under a supplier license issued to a holder of mining license prior to the coming into effective of this proclamation shall lapse after 120 days of the effective date of this Proclamation.

## 14. Application for License

Notwithstanding to the requirements stated under other laws, an application for license shall be made in writing and contain the following.

1. Where the application is for mineral supplier license;

a/ Name, occupational address and nationality of the applicant;

b/ The type of mineral that the applicant wishes to engage in;

c/ The location where the applicant purchases and sale the mineral;

d/ An evidence showing the permanent store and work place as to be determined by the type of the mineral;

e/ Business plan;

f/ An evidence showing the capital required for the implementation of the business plan based on the Commercial Laws;

2. Where the application is for mineral crafting license;

a/ The requirements under sub article 1 (a), (b), (e) and (f) of this Article;

b/ System of removing unnecessary by-products;

https://chilot.me

ሐ/ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ፣

፫. ማመልከቻው ለማዕድን ማጣራት ፈቃድ ሲሆን፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱት፣

ለ/ የማጣሪያ ተቋሙን ለማቋቋም ያለው ችሎታና ልምድ፣

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ፊደል ተራ (ሐ) የተጠቀሰውን፡፡

፬. ማመልከቻው ለማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ ሲሆን፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ፩ በ (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱትንና፣

ለ/ ማዕድናትን ለማቅለጥ ያለው የቴክኒክ ብቃት፣

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ (ሐ) የተጠቀሰውን፡፡

፭. ማመልከቻው ለማዕድን ንግድ ፈቃድ ሲሆን

ሀ / በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) (ሐ) ፣(መ) ፣ (ሠ) እና (ረ) ሥር የተመለከቱትን፤

ለ/ የሚሸጠውን ማዕድን ያለውን ጥራትና መጠን ለተጠቃሚዎች ወይም ለደንበኞች የሚያሳውቅበትን ሁኔታ፤

ሐ/ የማዕድን ንግድ የሚያከናውንበት ቦታ እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ፤

፮. ማመልከቻው ለማዕድን ላኪነት ሲሆን

ሀ/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) ፣ (ሐ) ፣ (መ) እና (ሠ) ሥር የተመለከቱትን፤

ለ/ ለመላክ ያቀደው ማዕድን የሚያገኝበት ቦታ፤

ሐ/ የዕደ ጥበብ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ ያለውን ፈቃድ ቁጥር፤

c/ An environmental impact assessment study which is prepared in accordance with Environmental Impact Assessment Proclamation.

3. Where the application is for mineral refining license;

a/ The requirements under sub article 1 (a), (b), (d), (e) and (f) of this Article;

b /The capacity and experience to establish the refining plant;

c/ The requirements under sub article 2 (c) of this Article;

4. Where the application is for mineral smelting license;

a/ The requirements mentioned under sub article 1 (a), (b), (d) (e) and (f) of this Article;

b/ Technical capacity to establish the smelting plant;

c/ The requirements mentioned under sub article 2 (c) of this Article;

5. Where the application is for Mineral transaction license

a/ The requirements mentioned under sub-article 1 (a), (b) , (c) , (d) , (e) and (f) of this Article

b/ System as to how he notifies the consumers on the quality and quantity of the mineral he sells;

c/ Evidence that shows the availability of work place to perform mineral transaction. ;

6. Where the application is for mineral exporting license

a/ the requirements mentioned under sub article 1 (a), (b) , (c) ,(d), (e) and (f)( of this Article ;

b/ source of the mineral he intended to export;

c/ the license number if he engages in mineral crafting;

https://chilot.me



**፲፭. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

፩. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለና አመልካቹ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ ፈቃዱን ይሰጠዋል፡፡

፪. የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም አመልካቹ በሕጉ መሰረት ፈቃድ ሊሰጠው የማይገባ ከሆነ ፈቃዱ አይሰጥም፡፡

፫. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃዱን የማይሠጥ ከሆነ በ ፲ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ከነምክንያቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፲፮. <u>ስለፈቃድ ዘመን እና እድሳት</u>**

፩. ማንኛውም ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡

፪. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ለማሳደስ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች ካሟላና የዚህን አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብ እና መመሪያዎችን እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች በመተላለፍ ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ለአንድ አመት ጊዜ የማሳደስ መብት ይኖረዋል፤

፫. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን ማብቂያ ላይ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፤ ሆኖም በቅጣት ሊታደስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

፬. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለዕድሳት በሚቀርብበት ወቅት የወቅቱን በጀት ዓመት ግብር ስለመክፈሉ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡



**15. <u>Issuance of License</u>**

1. The licensing authority may issue a license after ascertaining that the applicant has fulfilled all the requirements and upon payment of the prescribed license fee.

2. A license may not be granted if the submitted application is not accepted or the applicant is not eligible to get the license pursuant to the law.

3. If the licensing authority refuses to grant the license, it shall notify the decision and the reason for refusal to the applicant, in writing within 10 days.

**16. <u>Duration and Renewal of the License</u>**

1. Any license shall be valid for one year from the date of issuance.

2. The license may be renewed for one year, upon payment of the prescribed fee, if the licensee meets all requirements for renewal and is not in breach of any provision of this Proclamation or Regulation or Directives issued for the implementation of this Proclamation which constitutes ground for the revocation.

3. Any licensee shall renew his license at the end of each license period. However, it may be renewed with penalty.

4. Any licensee who wishes to renew his license shall produce tax clearance certificate for the budget year from tax office.

https://chilot.me

**፲፯. የባለፈቃድ ግዴታዎች**

፩.አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ/ እንደማእድኑ ዓይነት የገዛውን፣ ያስቀመጠውን፣ ያጣራውን፣ ያቀለጠውን፣ የሸጠውን ወይም ወደ ውጭ ሀገር የላከውን ማዕድን በተመለከተ መዛግብትና ማኅደር የመያዝ፤

ለ/ በየአመቱ የበጀት ዘመኑ በተጠናቀቀ በ ፵፭ ቀናት ውስጥ ያካሄደውን ግብይት በተመለከተ ለፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርት የማቅረብ፤

ሐ/ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች አካላት የወጡ የአሰራር፣ የደኅንነትና የጤንነት ደረጃዎች አፈጻጸም በተመለከተ በየሶስት ወሩ ሪፖርት የማቅረብ፤

መ/ በመመሪያ ከተወሰነው በላይ ማዕድን ያለማከማቸት፤

ሠ/ ሥራውን በሚያከናውንበት በማናቸውም ጊዜ ፈቃዱን እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይዞ የመገኘት ፤

ረ/ በፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰጪ ባለሥልጣን ወይም ሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ ለመቆጣጠር ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት በሚሰየም ተቆጣጣሪ ፈቃዱን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት ፤

ሰ/ የያዘውን ማዕድን ምንጭ ለተቆጣጣሪዎች የማሳየት ፡፡

ሸ/ የሥራ ቦታዉን ሲቀይር በቅድምያ ለፈቃድ ሰጪዉ አካል የማሳወቅ

፪. የአቅራቢነት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ/ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጠኑ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጋር በሚደረገው ስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ለባንኩ ወይም በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ፤



**17. Obligations of the Licensee**

1. Notwithstanding to obligations stipulated under other laws, Any licensee shall have the obligation:

a/ To maintain books and records regarding types of the mineral purchased, deposited, refined, smelted, sold or exported as the case may be;

b/ To report all transactions carried out to the licensing authority within 45 days of the end of each budget year;

c/ to report every 3 months on execution of all operational, safety and health standards set for by the ministry or other appropriate Government Authorities;

d/ not to hold mineral more than the amount prescribed by directives.

e/ to hold the license and certificate of competence at all times while carrying out his activity.

f/ to display the license when requested by the licensing or certificate of competence issuing authority or legally authorized inspector assigned to control illegal trade and contraband.

g/ to show the source of mineral to the inspectors.

h/ to notify the licensing authority if he changes his work place.

2. Mineral supplier licensee shall have the obligation to:

a/ Supply gold and silver to the bank or legally authorized entity every budget year an amount to be determined by an agreement with the licensing authority.

https://chilot.me



ለ/ ከወርቅና ከብር ውጪ ያሉ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት በሀገር ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ላላቸው የመሸጥ፣

ሐ/ የኮንስትራክሽን እና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሀገር ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ላላቸው ወይም ለተጠቃሚ የመሸጥ ፣

መ/ የሚያቀርባቸውን ማዕድናት ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን የማሳወቅ፣

ሠ/ ሥራውን የሚመራበት ቋሚ አድራሻ የማዘጋጀት እና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማሳወቅ፣

ረ/ ፈቃድ በወሰደበት ክልል ውስጥ ብቻ ማዕድን የመግዛት፣

ሰ/ ወርቅና ብር ሲሆን አቅራቢያው በሚገኘው ግዢ ማዕከል ባንክ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጠው አካል ድረስ፣ ከወርቅ ወይም ብር ውጪ ያሉትን የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን የላኪነት ፈቃድ ወይም መቅረጽ ባለፈቃድ እስካለበት ቦታ ድረስ፣ ሌሎች ማዕድናትን ቀጣይ ገዢ ወይም ተጠቃሚ እስካለበት ቦታ ድረስ ብቻ ይዞ የመንቀሳቀስ፣

ሸ/ ማዕድን ሲገዛና ሲሸጥ ሕጋዊ ደረሰኝ የመጠቀም፣

ቀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) መሰረት በየአመቱ ከሚያቀርበው ሪፖርት በተጨማሪ የገዛቸውንና የሸጣቸውን ማዕድናት በተመለከተ በየ ፫ ወሩ ለክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ሪፖርት የማቅረብ፡፡

፫. የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፦

ሀ/ ለሥራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወረቅ ወይም ብር ከባንክ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ብቻ የመግዛት፣

ለ/ የገዛውን ወርቅ ወይም ብር በጥሬ መልኩ ለማንኛውም ሰው ያለማስተላለፍ፣

ሐ/ ከወርቅና ብር ውጪ የሆኑ ሌሎች ማዕድናት ሲገዛ ምንጩ ሕጋዊ መሆኑን የማረጋገጥ፣

b/ Sell locally precious or semi-precious mineral, other than gold and silver, to the holder of a license pursuant to this proclamation.

c/ Sell locally construction and industrial minerals to the holder of a license or consumer.

d/ Notify the legal source and area of production of the mineral he supplies.

e/ Arrange permanent work place and inform the licensing authority.

f/ Purchase mineral only within the region where his license is issued.

g/ Transport gold or silver to the nearest bank or legally authorized entity, precious or semi-precious minerals, other than gold or silver, to the holder of export license or to the location of the holder of lapidary license, and other minerals to the place of the next purchaser or consumer.

h/ Use legal invoices while purchasing and selling mineral.

i/ Provide report of purchased or sold minerals every three months to the regional licensing authority In addition to the report submitted annually as per sub article 1 (b) of this Article.

3. Mineral crafting licensee shall have the obligation to:

a/ Purchase raw gold or silver only from bank or legally authorized entity;

b/ Not to transfer the gold or silver he purchased to any other person in its raw form.

c/ Verify that the source of the raw mineral is legal when he purchases minerals other than gold or silver.

https://chilot.me



መ/ በሚያመርታቸው የማዕድናት ውጤቶች ላይ ሊለዩ የሚችሉ የራሱ የሆነ ምልክት የማድረግ፣

ሠ/ ማንኛውም ሰው ምርቱን በሚገዛበት ወቅት ምልክቱን እንዲለይ፣ ጥራቱንና ብዛቱን እንዲያውቅ የማድረግና ለዚህም ለተገልጋዩ ማረጋገጫ የመስጠት፣

ረ/ በመመሪያ ከተወሰነው በላይ የወርቅና ብር ክምችት ሲኖረው ለባንኩ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ላለው አካል የመሸጥ፡፡

፬. የማዕድን ማጣራት ባለፈቃድ በሚያጣራው ማዕድን ላይ ሊለዩ የሚችሉ የራሱ የሆነ ምልክት የማድረግ፣ ጥራቱንና መጠኑን እንዲታወቅ የማድረግና ለዚህም ለተገልጋዩ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።

፭. የማዕድን ማቅለጥ ባለፈቃድ በሚያቀልጠው ማዕድን ምርት ላይ ሊለዩ የሚችሉ የራሱ የሆነ ምልክት የማድረግ፤ መጠኑን የመግለጽ ለዚህም ለተገልጋዩ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።

፮. የማዕድን ንግድ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ/ ከዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች የሚረከባቸውን ምርቶች ተገቢው ምልክት እንዳላቸው የማረጋገጥ ፤

ለ/ ከዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች የሚረከባቸውን ምርቶች ይዞታቸውን ያለመቀየር ወይም ከሌላ ማዕድናት ጋር ያለመቀላቀል፤

ሐ/ ተጠቃሚ ወይም ደንበኛው ከእሱ የሚገዛውን ምርት ጥራትና መጠን ማወቁን የማረጋገጥ ለዚህም ማረጋገጫ የመስጠት፡፡

፯. የማዕድን ላኪነት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የሚልከው ጥሬ ማዕድን ከሆነ ማዕድኑን ያገኘበትን ሕጋዊ ምንጭ የማሳየት፤



d/ Put an identifiable mark of his own on each mineral he produces.

e/ Make sure that any consumer identifies the mark, know or understand the quality and quantity of the product he produces and provide proof to that effect.

f/ Sell to the bank or legally authorized entity when he possesses gold or silver above the amount permitted by Directive.

4. Mineral refining licensee shall have the obligation to put an identifiable mark of his own on each mineral he refines, make sure that any consumer identifies the mark, know or understand the quality and quantity of the product he refines and provide proof to that effect.

5. Mineral smelting licensee shall have the obligation to put an identifiable mark of his own on each mineral he smelts, make sure that any consumer identifies the mark, know or understand the quantity and quality of the product he smelts and provide proof to that effect.

6. Mineral transaction licensee shall have the obligation to:

a/ To make sure that all product he receives from the holder of crafting license has got the proper mark;

b/ Not to alter or blend the mineral he brought from the holder of crafting license with other types of mineral;

c/ To make sure that the user or customer knows volume and the quality and quanity of his products and provide proof to that effect.

7. Mineral export license shall have the obligation to:

a/ Demonstrate the legal source of the mineral when he exports raw mineral,

https://chilot.me

ለ/ የሚልከው ሙሉውን ወይም በከፊል ያለቀለት ማዕድን ከሆነ ሕጋዊ ምንጩን ከማሳየት በተጨማሪ ማዕድኑን ያሰናዳውን ሰው ስምና የፈቃድ ቁጥሩን የያዘ ማስረጃ የማቅረብ ፤

ሐ/ ማዕድናት ወደ ውጪ ሲልክ ተገቢውን የባንክ ሕግ የማክበር፤

መ/ ወደ ውጪ የሚላከው ወርቅ ወይም ብር ሲሆን በጌጥ መልክ የተሰሩ የመጨረሻ ቅርፃቸውን የያዙ ብቻ የመላክ፤

ሠ/ ጥሬ ወይም በከፊል ያለቀለት ወይም የመጨረሻ ቅርጹን የያዘ ማዕድን ሲገዛና ሲሸጥ ሕጋዊ ደረሰኝ የመጠቀም፤

ረ/ እንደ አግባብነቱ የገዛውን ወይም ወደ ውጭ ሀገር የላከውን ማዕድን በተመለከተ መዛግብትና ማኅደር የመያዝ፡፡

## ፲፰. ፈቃድ ማስተላለፍ

ከማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ በስተቀር ሌሎች ፈቃዶችን ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስፈቀድ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ፈቃድ የሚተላለፈው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

## ፲፱. ፈቃድ ስለማገድና ስለመሰረዝ

፩. አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ባለፈቃዱ፡-

ሀ/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መያዝ የሚገባውን መዛግብትና ማኅደሮች ካልያዘ፤

ለ/ ሕጋዊ የግብይት ሰነድ ሳይጠቀም ማዕድን ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤

ሐ/ በፈቃዱ ላይ ከተገለፀው ክልል ወጪ ሲሰራ ከተገኘ፤



b/ Reveal a document showing the name and license number of the licensee who processed the mineral when the export is processed or semi processed mineral in addition to demonstrating the legal source.;

c/ Respect the relevant laws of the bank while exporting minerals;

d/ To export only a processed ornament in its final shape where the export is gold or silver,

e/ Use legal invoice, when he purchases or sales mineral in raw or partially semi processed or in final shape.

f/ Have books and records of the minerals he purchased or exported, as the case maybe.

## 18. Transfer of License

Any license, other than supplier license, may be transferred with prior consent of the licensing authority. The license is transferred according to provisions of trade registration and licencing proclamation.

## 19. Suspension and Cancellation of the License

1. Without prejudice to other relevant laws, the license issued pursuant to this proclamation shall be revoked where the holder of the license:

   a. Fails to maintain books and records as required by relevant laws.

   b. Purchase from, sale or transfer a mineral to a person who does not have a mining license.

   c. Engage in mineral transaction activities not specified in the license;

https://chilot.me



መ/ ተቆጣጣሪዎች ወደ ሥራ ቦታ እንዳይገቡ ከከለከለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም መዝገቦች፣ ማኅደሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያዩ ካደረገ፤ ወይም

ሠ/ የአካባቢን፣ ጤንነትንና ደኅንነትን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ከጣሰ፤ፈቃዱ ይታገዳል፡፡

፪ አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ባለፈቃዱ፡-

ሀ/ ባለፈቃዱ ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ፤

ለ/ ፈቃዱን ያገኘው የሀሰት መረጃዎችን በማቅረብ ሲሆን፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱን ሳያሳድስ ከቀረ፤

መ/ በፈቃዱ ላይ ባልተመለከቱ ማዕድናት ግብይት ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤

ሠ/ በፈቃዱ የተፈቀደለትን ማዕድን ፈቃድ ከሌለው ሰው ከገዛ ወይም የገዛውን ማዕድን ፈቃድ ለሌለው ሰው ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤

ረ/ በተሰጠው ፈቃድ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ ሕገወጥ ግብይት ካካሄደ ወይም የማጭበርበር ተግባር ከፈጸመ፤

ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃድ ለማገድ ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

d. An holder of a licence prohibit the inspectors not to enter and render their activites or unwilling to do so or fails to maintain books and records and other documents;

e. Violates safety and environmental protection obligations,his licence shall be suspended.

2. Notwithstanding to relevant laws , the license holder:-

a. Has ceased to operate his business,

b. Is found to have obtained his licences by submitted false documents,

c. Has failed to to renew his business licence pursuant to this proclamation,

d. An holder to have engaged in unauthorized activity which is not envisaged in the licence,

e. An holder of the licence of minerals buying or selling or transfer a mineral permited in his certificate of competence to a person who has no licence,

f. Engage in illicit transaction or fraudulent activites in connection with the work stated in his licence,

g. Fails to rectify reasons of suspension of license specified under sub article 1 of this Article with in the period that will be determined by the Regulation.His licence shall be cancelled.

https://chilot.me



**፳. ስለፈቃድ ክፍያ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማሳደስና ለሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ በፈቃድ ሰጪዉ ባለስልጣን እየተሰራበት ባለው ሕግና አሰራርተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

**፳፩. የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት ዓይነቶች**

በማዕድን ግብይት ስራ የሚከተሉት የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀቶች ይሰጣሉ፡-

፩. የማዕድን አቅራቢነት ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

፪. የማዕድን ዕደ ጥበብ ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

፫. የማዕድን ማጣራት ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

፬. የማዕድን ማቅለጥ ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

፭. የማዕድን ንግድ ብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

፮. የማዕድን ላኪነት ብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

**፳፪. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

፩. ማንኛውም በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተገለጹትን ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ በዚህ አዋጅ የተጠቀሰውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡

**20. License Fees**

Fees payable for the issuance, renewal or other related services of license pursuant to this proclamation shall be determined by licensing authority pursuant to the applicable laws.

## CAPTER TWO

## CERTIFICATE OF COMPETENCE

**21. Types of Certificate of Competence**

The following certificate of competence may be issued for mineral transaction undertakings:

1. Mineral supplier Certificate of Competence;

3. Mineral crafting Certificate of Competence;

4. Mineral refining Certificate of Competence;

5. Mineral smelting Certificate of Competence

6. Mineral Transaction Certificate of Competence

7. Mineral Export Certificate of Competence .

**22. Eligibility for Certificate of Competence**

1. Any person, who qualifies to carryout trade in accordance with relevant laws and fulfills the requirements under this Proclamation, Regulation and Directives issued for the implementation of this proclamation, may acquire any certificate of competence referred in this proclamation.

https://chilot.me



፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ/ የማዕድን ንግድ ወይም የላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለውጭ ባለሀብት አይሰጥም፤

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሰው የምስክር ወረቀት ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ሌላ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም፤

፫. በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተገቢ ሁኔታ በመሟላት ፈቃድ መውሰድ አለበት፡፡

## ፳፫. ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማመልከቻ

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ መያዝ ያለበት መስፈርት እንደአግባቡ ፍቃድ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ የተደነገጉት እና ሌሎች ሚኒስትሩ በመመርያ የሚወስናቸው ይሆናል፤

## ፳፬. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለና አመልካቹ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪. የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም ለአመልካቹ በሕጉ መሰረት የምስክር ወረቀት ሊሰጠው የማይገባ ከሆነ የምስክር ወረቀቱ አይሰጥም፡፡



2. Notwithstanding the provision of sub article (1) of this article;

a/ Mineral transaction or exporter certificate of competence shall not be issued to foreign investor.

b/ No person whose certificate of competence has been suspended pursuant to this Proclamation may hold another certificate of competency for two years following such Suspension;

3. Any person who has been granted with certificate of competence pursuant to this roclamation, before commencement of the work, shall acquire a license from the appropriate Government Office upon fulfillment of the requirements.

## 23. Application for Certificate of Competence

An application for certificate of competence shall be made in writing and contain as the case may be the requirements for license stipulated under article 14 and other requirements to be decided by Directive to be issued by the Ministry.

## 24. Issuance of Certificate of Competency

1. The certificate of competence issuing authority may issue a certificate of competence after ascertaining that the applicant has fulfilled the requirements upon payment of the prescribed fee.

2. Where the application is denied or the applicant is not eligible to receive the certificate of competence pursuant to the law, the certificate shall not be issued.

https://chilot.me



፫. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ከሆነ በ ፭ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ከነምክንያቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፳፭ ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዘመን እና እድሳት

፩.ማንኛውም የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡

፪. የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች ካሟላና የዚህን አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብ እና መመሪያዎችን በመተላለፍ ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ለአንድ አመት ጊዜ የማሳደስ መብት ይኖረዋል፤

፫. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት በያንዳንዱ የምስክር ወረቀት ዘመን ማብቂያ ላይ ማሳደስ አለበት፡፡ ሆኖም በቅጣት ሊታደስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡አለበት፡፡ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፬. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት ለዕድሳት በሚቀርብበት ወቅት የወቅቱን በጀት ዓመት ግብር ስለመክፈሉ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## ፳፮. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድና ስለመሰረዝ

፩. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የምሥክር ወረቀት ባለቤቱ-

ሀ/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መያዝ የሚገባውን መዛግብትና ማኅደሮች ካልያዘ፤

ለ/ ሕጋዊ የግብይት ሰነድ ሳይጠቀም ማዕድናትን ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤

3. If the licensing authority refuses to grant the certificate, it shall notify the decision and the reason for refusal to the applicant, in writing within 5 days.

## 25. Duration and Renewal of Certificate of Competence

1. Any certificate of competence shall be valid for one year from the date of issuance.

2. The certificate may be renewed for one year if the holder of certificate meets all requirements and is not in breach of any provision of this proclamation or Regulation or Directives issued for the implementation of this Proclamation which constitutes grounds for the suspention and upon payment of the prescribed fee.

3. All certificates shall be renewed at the end of every period of certificate of competence. However, it may be renewed with penalty.The detailed shall be determined by the Regulation.

4. Any holder of certificate who wishes to renew his certificate shall produce tax clearance certificate for the budget year from tax office.

## 26. Suspension and Cancellation of Certificate of Competence

1.The certificate of competence issued pursuant to this Proclamation shall be suspended where the holder of the certificate:

a. Fails to maintain books and records as required by relevant laws;

a. Purchase, sale or transfer mineral without legal transaction document.

https://chilot.me



ሐ/ ተቆጣጣሪዎች ወደ ሥራ ቦታ እንዳይገቡ ከከለከለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም መዝገቦች፣ ማኅደሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያዩ ካደረገ የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል፡፡

፫ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤቱ፡-

ሀ/ ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ፤

ለ/ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው የሀሰት መረጃዎችን በማቅረብ ከሆነ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱን ሳያሳድስ ከቀረ፤

መ/ በምስክር ወረቀት ላይ ባልተመለከቱ ማዕድናት ግብይት ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤

ሠ/ በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተፈቀደለትን ማዕድን ፈቃድ ከሌለው ሰው ከገዛ ወይም ፈቃድ ለሌለው ሰው ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤

ረ/ በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ ሕገወጥ ግብይት ካካሄደ ወይም የማጭበረበር ተግባር ከፈጸመ፤

ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌዎች መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማገድ ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

## ፳፯. ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ክፍያ

በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀት ለመስጠት፣ ለማሳደስ ወይም ለሌሎች ተያያዥ አገልግሎት የሚጠየቀው ክፍያ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሲሆን ከዚህ በፊት ይሰራባቸው የነበሩት

c. Holder of a license if he prohibit the inspectors not to to enter or unwilling to show books and records or other documents.

3. The certificate of competence issued pursuant to this Proclamation shall be cancelled where the holder of the certificate:

a. Has ceased to operate his business,

b. Is found to have obtained his licences by submitted false documents,

c. Has failed to to renew his certificate of competence pursuant to this proclamation,

d. An holder to have engaged in unauthorized activity which is not envisaged in the certificate of competence,

e. An holder of the licence of minerals buying or selling or transfer a mineral permited in his certificate of competence to a person who has no licence,

f. Engage in illicit transaction or fraudulent activites in connection with the work stated in his certificate of competence,

g. fails to rectify reasons of suspension of certificate of competence specified under sub Article 1 of this Article with in the period that will be determined by Regulation.

## 27. Certificate of Competence Fees

Fees payable for the issuance of certificate of competence, renewal or other related services pursuant to this Proclamation shall be determined in accordance with regulation to be issued for the implementation of this

https://chilot.me



የክፍያ ሥርዓቶች ደንቡ ሥራ ላይ እስከሚውልበት ቀን ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

proclamation; however previous fee payment procedures shall remain applicable until the Regulation becomes effective.

## ክፍል ሦስት

## ስለ አስተዳደር

### ፳፰. ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠትና የማስተዳደር ሥልጣን

የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

ሀ/ ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የመሰረዝ እና የግብይት ሥርዓቱ በአግባቡ መከናወኑንየመከታተልና የመቆጣጠር፤

ለ/ የማዕድን ማጣራት ፈቃድ፣ የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ማቅለጥ ፈቃድ እናየማዕድናት ላኪነት ፈቃድ የመስጠት፤

ሐ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማዕድናት ግብይት ሕጋዊነትን የመቆጣጠር እና ሕገወጥ የማዕድናት ግብይት ፈጻሚዎች ለሕግ እንዲቀርቡ የማድረግ፡፡

መ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊነቱ ለታመነባቸው ማዕድናት የገበያ ማዕከል የማቋቋም፤

፪. የሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማዕድን ማጣራት ብቃት ማረጋገጫ፣ የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ማቅለጥ ብቃት ማረጋገጫ እና የማዕድናት ላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

ለ/ የማንጠር፣ የመቅረጽ፣ የማጣመር እና የማጣራት ሥራዎች የሚያከናውኑበትንየአሠራር ደረጃ የማውጣትና የማስፈጸም፤

ሐ/ ከሀገር በሚወጡና በሚገቡ ማዕድናት ላይ የቤተ-ሙከራ ምርመራ መደረጉን የማረጋገጥና የቁጥጥር ፍተሻ የማድረግ፤

## PART THREE

## ADMINISTRATION

### 28. Power of Issuance of Licence and Certificate of Competence and Management

The authority has the following Power and Duties.

a/ Issue, renew, revoke the license and monitor the performance of the activities;

b. Issue mineral refining, smelting for metallic and associated minerals and mineral exporter certificate of competence;

c. In collaboration with relevant organs, monitor the legality of minerals transaction and bring those engaged in illegal minerals transaction before the court of law.

d. Establish minerals market center subject to the importance of the mineral.

2.The Ministry has the following Power and Duties;

a. Issue mineral refining, smelting for metallic and associated minerals and mineral exporter certificate of competence;

b. Set and enforce standards in which smithery, lapidary, combining and refining activities are carried out.

c. Approve and conduct inspection whether a laboratory test is made on export and import minerals.

https://chilot.me



መ/ በአለም አቀፍ ደረጃ ዋጋቸው በግልጽ የማይታወቅ ማዕድናት ለሽያጭ ሲቀርቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዋጋቸውን የመወሰን፤

ለ/ በደረጃ ተለይተው ለውጭ ገበያ ለሚቀርቡ ማዕድናት ደረጃ ማውጣት፡፡

፫. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ውስጥ አስፈላጊነቱ የታመነበትን ውስን ሥራ አግባብነት ላላቸው የፌዴራልና የክልል አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ ( ለ )እና ንዑስ አንቀጽ ፪ ( ለ )ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶች በክልሎች ይሰጣሉ፡፡

**፳፱. <u>ስለ ክትትልና ቁጥጥር</u>**

፩. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለስልጣን የሚመድባቸው ተቆጣጣሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክርወረቀት ባለቤት ስራ ቦታ የመግባት፣ ናሙና የመውሰድ፣የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን የማከናወን ስልጣን ይኖራቸዋል።

፪.ተቆጣጣሪዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሊኖራቸው የሚገቡ ግዴታዎች በደንብ ይወስናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፴. <u>የባንክ ኃላፊነት</u>**

ባንኩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. በባሕላዊና በልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የሚመረተውን የወርቅ ወይም የብር ማዕድናት ከአምራቾች ወይም ከአቅራቢዎች የመግዛት፣

፪. የዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች የሚያስፈልጋቸውን የወርቅ ወይም የብር ማዕድናት በሽያጭ የማቅረብ፣



d/ Work together with relevant entities and set the price of minerals if the price is not internationally determined.

b. Determine for the minerals to be exported .

3.The Ministry Shall Delegate some of its Powers and Functions from those specified under this proclamation that is considered necessary to appropriate Federal and Regional Organs.

4. Licenses and Certificate of Competences other than specified under sub Article 1(b) and 2(b) of this Article will be given by the Regions.

**29. <u>Inspection and Regulation</u>**

1. Those Inspectors Who Is Deployed by the certificate of Competence Issuing Authority shall have the power to enter in to the working sites of the holder of certificate of competence, take samples and undertake follow up and inspection activities.
2. The Duties of Inspectors while undertaking their activities will bedetermined by Regulation.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**30.<u>Responsibility of the Bank</u>**

The Bank shall have the following Duties and Responsibilities;

1. Purchase gold or silver produced by the holders of artisanal or special small-scale mining or supplier license.

2. Make available gold or silver for sell to the holder of crafting license.

https://chilot.me



፫. አቅራቢዎችን ሊያበረታቱ የሚችሉ የክፍያ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ፣ የግገር ማዕከላት ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና የግብይት ሥርዓቱ የተቀላጠፈ እንዲሆን የማድረግ፣

3. Facilitate better payment condition to encourage the suppliers, make accessible market centers and expediting the transaction system.

## ፴፩. የማዕድናትን ናሙናዎች በጊዜያዊነት ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ

፩. የማዕድን ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ ወርቅና ብር ወይም በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ያለቀላቸው የሌሎች ማዕድናት ናሙናዎችን ለማስተዋወቅ ዓላማ በባንኩ መመሪያ መሠረት በጊዚያዊነት ወደ ውጭ ሀገር መላክ ይችላል፤

፪. የማዕድናት ላኪነት ፈቃድ ባለቤት የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ ወርቅና ብር እንዲሁም ሌሎች ማዕድናትን በጥሬ፣ በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ የተሰናዱ ናሙናዎችን በባንኩ መመሪያ መሠረት ለማስተዋወቅ ዓላማ በጊዚያዊነት ወደ ወጭ ሀገር መላክ ይችላል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከተው ቢኖርም የዕደ ጥበብ ወይም የላኪነት ፈቃድ ያለው ሰው የመጨረሻ ቅርጽ የያዙ ወርቅ እና ብር እንዲሁም ሌሎች ማዕድናትን በጥሬ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተሰናዳውን ለማስተዋወቅ ዓላማ ወደ ውጪ መላክ የፈለገ ከሆነ በሚከተለው ሥነ ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡-

ሀ/ አመልካቹ የዓለም አቀፍ ዋጋ ላላቸው በዋጋቸው እንዲሁም ዓለም አቀፍ ዋጋ ከሌላቸው ደግሞ ሚኒስቴሩ በሚተምነው መሠረት የባንክ ዋስትና ያስይዛል፤

ለ/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የማዕድናት ናሙናዎቹ ወደ ውጭ ሀገር ሲላኩና ወደ ሀገር ውስጥ ሲመለሱ ዓይነታቸውን፣ ጥራታቸውንና መጠናቸውን ያረጋግጣል፤

## 31. Temporary Export of Samples of Minerals

1. A holder of mineral crafting license shall have the right to temporarily export sample of gold or silver in their final shape; other processed or semi processed minerals for the purpose of promotion in accordance with the Directive of the bank,

2. A holder of mineral exporter license shall have the right to temporarily export sample of gold or silver in their final shapes; other minerals in raw, semi processed or processed form for the purpose of promotion in accordance with the Directive of the bank,

Notwithstanding to the provision of sub article (1) and (2) of this Article, a holder of mineral crafting or exporter license to export sample of gold or silver in their final shape; other minerals in raw, semi processed or processed form shall be in accordance with the following procedure;

a/ The applicant shall produce a bank guaranty equivalent to the amount of their current world market price, where they are quoted in the International Market, or in the absence of such price, in an amount to be specified by the ministry.

b/ The Ministry shall certify the type, quality and quantity of samples of minerals before export and upon their return in accordance with this Article.

ሐ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደ ውጭ ሀገር የተላኩት የማዕድናት ናሙናዎች በዘጠና ቀናት ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ካልተመለሱ ባንኩ እና ሚኒስቴሩ በባንክ የተያዘው የዋስትና ገንዘብ ወደ ሚመለከተው የመንግሥት አካል ገቢ እንዲሆን ያደርጋሉ፤

መ/ ተመላሽ የሆኑት ናሙናዎች ቀደም ሲል ከተላኩት ጋር በመጠን፣ በጥራት ወይም በዓይነት አንድ ዓይነት አለመሆናቸውን ሚኒስቴሩ ካረጋገጠ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ሐ/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም እንደ ማዕድኑ ዓይነትና ባሕሪይ በምርመራ ወቅት ከመጠናቸው የተወሰነውን ያህል ሊቀንሱ የሚችሉ ማዕድናት ዝርዝር በደንብ ይገለጻል፡፡

## ፴፪. <u>እሴት መጨመር</u>

ዝርዝሩ እንደ ማዕድናቱ እና እንደ ፈቃዱ ዓይነት የሚወሰን ሆኖ የግብይት ባለፍቃድ ማዕድናት በተሻለ ዋጋ መሸጥ እንዲችል፣የማለስለስ ፣የማስዋብ የማጣመር፣ ቅርጽ የማውጣት እና ሌሎች መሰል ተግባራትን ማከናወን አለበት፡፡

## ፴፫. <u>ተረፈ ምርት</u>

፩.የዕደ ጥበብ ፣ የማጣራት፣ የማቅለጥ ሥራዎች ሲከናወኑ የሚፈጠሩት ዋጋ የማያወጡ የአካባቢ ብክለት የሚያስከትሉ ተረፈ ምርቶችን ባለፈቃዱ በአግባቡ ማስወገድ አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ተረፈ ምርት ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ ጥቅም ላይ የሚውልበትን አግባብ ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## ፴፬. <u>ስለግል መጠቀሚያ</u>

ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳያስፈልገው የመጨረሻ ቅርጹን የያዘ የግል መጠቀሚያውን ማዕድን መያዝ፣ ማጓጓዝ፣ ይዞ ከሀገር መውጣት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ስለሚችልበት ሁኔታ፣ መጠንና ጥራት በደንብ ይወሰናል።



c/ Where the sample of the minerals exported pursuant to this Article fails to return fully or partially within 90 days from the date of their export, the bank and the ministry shall facilitate the deposit of the bank guaranty to the relevant Government Authority,

d/ Where the Ministry verifies that the returned samples of minerals are not identical in quantity, quality or type with the exported samples, the Provision of paragraph (c) of this sub article shall apply. However, subject to the type and character of the minerals, the list of the mineral that decreases in size during examination shall be prescribed by the Regulation.

## 32. <u>Adding of Values</u>

As the detailes will be determined based on the types of minerals, to enable the trade licence holder to sale it in better price he shall mold, polish, décore and other similar activites.

## 33. <u>By-products</u>

1. The licensee shall discard by-products from crafting; refining and smelting that do not have value and have cause environmental pollution.

2. Where the by products mentioned under sub article (1) of this Article is valuable, the Ministry shall determine by Directive on how such by product can be used.

## 34. <u>Personal Use</u>

The quantity and quality of minerals in their final shape for personal use that any person may hold, transport, carry abroad or bring from abroad without obtaining a license shall be prescribed by Regulation.

**፴፭. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን በማስፈጸም ሂደት አግባብ ካለው ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፴፮. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>**

ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

፩. በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ያለቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተሰጠ የፀና ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የማዕድን ግብይት ማከናወን፤

፪. ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ያልተመለከቱትን ሥራዎች ማከናወን፤

፫. የአቅራቢነት ባለፈቃድ ወርቅ ወይም ብርን ከባንኩ ወይም በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ውጭ ማስተላለፍ፣ የተሳሳተ ጥራት ያለው ወርቅ ወይም ብር መሸጥ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ለባንኩ ወርቅ ወይም ብርን ከመሸጥ ጋር በተያያዘ የማታለል ተግባር መፈፀም፤

፬. ማንኛውም የማዕድናት ንግድ ፍቃድ ባለቤት አግባብ ባለው የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ያልተመረተን ምርት መሸጥ፣ በዕደ ጥበብ ባለፈቃድ የተመረተን ምርት ጥራቱን ወይም መጠኑን በሚያበላሽ መልኩ መቀያየር፤ ወይም ተጠቃሚ ወይም ደንበኛ የሚገዛውን ምርት ጥራትና መጠን ሊገባው ወይም ሊያውቀው በማይችለው ሁኔታ ማከናወንና የጽሑፍ ማረጋገጫ መግለጫ አለመስጠት፤

፭.ማንኛውም የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ከባንክ ወይም ሌላ ሕጋዊ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ውጭ ወርቅና ብርን መግዛት ወይም የገዛውን ወርቅና ብር በጥሬ መልኩ ለሌላ ማስተላለፍ፤

**35. <u>Duty to Cooperate</u>**

Any person has the duty to respect the implementation of this Proclamation and state of emergency measures taken by the emergency command post and law enforcement organ or its officials and cooperate there with.

**36.<u>Prohibited Activities</u>**

The following activities are prohibited;

1. Conducting transaction of minerals without obtaining valid license pursuant to this Proclamation and other relevant Laws;
2. Any holder of a license undertakes activities not indicated in the license or certificate of competence;
3. Any holder of a supplier license to transfer gold or silver to another person other than the bank or legally authorized organ, to sell an erroneous quality of gold or silver, or in any form to deceive the bank or legally authorized organ in the sale of such minerals;
4. Any holder of mineral transaction license to sell products not produced by the holder of crafting license, to modify products produced by the holder of crafting license with a view of compromising the quality or quantity of the product, to sell a product to consumers or users in a way they could not understand or know the quality and quantity, and not providing written proof of the description;
5. Any holder of crafting license to purchase raw gold or silver from other than the bank or legally authorized organ or transfer the same to any other person;

፮. ማንኛውም ባለፈቃድ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ማድናትን በመመሪያ ከሚወሰነው በላይ ማከማቸት፤

፯. ማንኛውም የላኪነት ወይም የዕደ ጥበብ ፈቃድ ባለቤት ለማስተዋወቅ ወይም ለየቤተ ሙከራ ፍተሻ ተግባር በጊዜያዊነት ከሀገር ያወጣቸውን የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት በዚህ አዋጅ ድንጋጌ ከተመለከተው ውጪ ሳይመልስ መቅረት፤

፰. ማንኛውም የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ በሚያመርታቸው ጌጣጌጦች ላይ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ተገቢውን ምልክት አለማድረግ ወይም የሚሸጣቸውን ምርቶች ተጠቃሚ ወይም ደንበኛው ጥራቱንና መጠኑን ሊገባው ወይም ሊያውቀው በማይችልበት ሁኔታ ማድረግና ተገቢውን የጽሑፍ ማረጋገጫ አለመስጠት፤ጥራት የሚያጎድሉ ባዕድ ነገሮችን መጨመር

፱. የላኪነት ፈቃድ ባለቤት የቤተ ሙከራ ውጤቱ የማይታወቅ ጥራቱ የተጓደለ ማዕድን ለሽያጭ ወይም ለማስተዋወቅ ዓላማ ወደ ውጭ መላክ፤

፲. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረትና በኢንዱስትሪው የሚፈለገውን ተገቢውን የቴክኒክ ዝግጅት ሳያደርጉ የዕደ ጥበብ ሥራውን ማከናወን፤

፲፩. በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ስለደህንነትና ስለአካባቢ ጥበቃ የወጡትን የአሰራር ደረጃዎችን መጣስ፤

፲፪. ማንኛውም የማዕድን ማጣራት ፈቃድ ባለቤት የተሳሳተ የማጣራት ውጤት ማስተላለፍ ወይም የማጣራት ሥራውን ከተገቢው ደረጃ በታች ማከናወን፤

፲፫. በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሰረት ለግል መጠቀሚያ ከተፈቀደው በላይ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ከሀገር ማውጣት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፤



6. Any holder of a license to store precious or semiprecious minerals more than the amount to be determined by directive;

7. Any holder of mineral exporter or crafting licence fails to return precious or semi-precious minerals he temporarily exported for promotion or laboratory test in violation of the provisions of this Proclamation;

8. Any holder of crafting license to produce, to sell or to transfer of ornaments without having the proper producer mark on it or put the sign in a way that the quality and quantity cannot be understood by consumer or user, and not provide written proof of the description and add impurities which are lower in quality;

9. Any holder of mineral exporter license to export mineral which is lower in quality for sale or promotion purpose without having a laboratory result.

10. To Undertake crafting activity without having due te preparation as required by the industry and according appropriate provision of this proclamation.

11. To Violate safety and environmental protection operating standard set by the ministry or other appropriate Government Authorities.

12. Any holder of refining license to communicate erroneous refining results or to conduct the refining below the required standard.

13. To Hold, to store, to transport, to carry out of the country or to bring from abroad precious or semi-precious mineral for personal use exceeding the limit prescribed under this Proclamation or Regulation to be issued.

፲፬. ማኛውም የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ ባለቤት ከማዕድን ማቅለጥ ጋር በተያያዘ ሥራውን በአግባቡ አለማከናወን ወይም የማታለል ተግባር መፈጸም፣

፲፭. የዚህ አዋጅ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጣ ደንብ፣ መመሪያ መጣስ፡፡

## ፴፯. ቅጣቶች

፩. ማንኛውም ሰው ተገቢ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው፡-

ሀ/ በከበሩ ወይም በከፊል በከበሩ ወይም ብረት ነክ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማራ በእጁ የሚገኘው ማዕድናትና ተያያዥ መሣሪያዎች ወይም ማሽኖች የሚወረሱበት ሆኖ ከ ፶ሺ - ፻ሺ ብር ገንዘብ ቅጣት እና እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ከተጠቀሰው ማዕድን ውጭ በሌሎች የማዕድን ዓይነት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማራ በእጁ የሚገኘው ማዕድናት የሚወረሱበት ሆኖ ከ ፴ሺ - ፶ሺ ብር ይቀጣል፤እና እስከ ፩ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

፪. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፪፣ ፮ እና ፯ ሥር የተደነገገውን የተላለፈ ከብር ፴ሺ ብር - ፶ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ እና እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

፫. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፭ ሥር የተደነገገውን የተላለፈ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች እንዲሁም ማዕድኑ የሚወረስና ድርጅቱ የሚዘጋ ሆኖ ከብር ፻ሺ - ብር ፻፶ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ እና እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

14. Any holder of mineral smelting license not to perform properly or act decisively in relation to his duty of smelting,

15. Violates Regulation, Directives and Provisions which are necessary to implement this proclamation.

## 37. Penalties

1. Any person who engages in the transaction of minerals without having the proper license or certificate of competence;

a/ Where it is a transaction of precious or semi-precious or metallic minerals, his minerals and any associated equipment or machine shall be confiscated and shall be punishable with a fine of 50,000 – 100,000 Birr and an imprisonment not more than 7 years;

b/ Where it is a transaction of minerals other than those mentioned under sub article 1 (a) of this Article, his minerals shall be confiscated and shall be punishable with a fine of 30,000 – 50,000 Birr; and an imprisonment not more than 1 years;

2. A holder of a license who breaches the Provision set under sub article 2, 6 and 7 of Article 36 of this proclamation shall be punishable with a fine of 30,000 – 50,000 Birr and an imprisonment not more than7 years;

3. A holder of a license who breaches the provision set under sub article 3 and 5 of Article 36 of this Proclamation, his minerals and any associated equipment or machineries shall be confiscated, his business shall be closed and shall be punishable with a fine of 100,000 – 150,000 Birr and an imprisonment not more than 10 years.

https://chilot.me



፬. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፬፣ ፰፣ ፱፣ ፲ እና ፲፪ ሥር የተደነገገውን የተላለፈ ከብር ፶ሺ- ብር ፹ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

፭. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፲፩ ሥር የተደነገገውን የተላለፈ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጉዳይ ላይ የተቀመጡትን የጥፋት ውሳኔዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፤

፮. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፲፫ የተደነገገውን የጣሰ ማዕድኑ ይወረሳል፡፡

፯. ማንኛውም የማዕድን ማቅለጥ ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፲፬ የተደነገገውን የማታለል ተግባር ከፈፀመ ከብር ፻ሺ- ብር ፻፶ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

፰. ማንኛውም የማዕድን ማቅለጥ ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ ፲፬ የተደነገገው ሥራውን በአግባቡ ባለማከናወን ለሚያደርሰው ጉዳት ከ ፶ሺ- ብር ፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፱. ማንኛውም የማንጠር ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ከግለሰብ በግዢ የሚሰበስባቸውን የተበላሹ ወይም የተሰበሩ የወርቅና ብር መጠን በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ሪፖርት አለማድረግ ከብር ፳ሺ- ብር ፴ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና እስከ ፫ ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

4. A holder of a license who breaches the provision set under sub article 4, 8, 9, 10 and 12 of Article 36 of the proclamation shall be punishable with a fine of 50,000 – 80,000 Birr and an imprisonment not more than10 years;

5. A holder of a license or a certificate of competence who breaches the provision set under sub article 11 of Article 36 of this proclamation shall be punishable pursuant with proclamation which is implemented on Environmental Impact Assesment;

6. A holder of a license who breach the provision set under sub article 13 of Article 36 of this proclamation, his minerals shall be confiscated;

7. A holder of mineral smelting license who deceived his customer as provided under sub article 14 of Article 36, shall be punishable with a fine of 100,000 – 150,000 Birr and an imprisonment not more than 10 years;

8. A holder of mineral smelting license who failed to perform his activity as provided under sub article 14 of Article 36 of this proclamation and caused damage, shall be punishable with a fine of 50,000 – 100,000 Birr;

9. Any holder of smithery license who fails to submit report of the amount of used or broken gold or silver that he purchased as per this proclamation c, shall be punishable with a fine of 20,000 – 30,000 Birr and an imprisonment not more than 3 years.

https://chilot.me



**፴፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ከከበሩ ማዕድናት ዉጪ በሆነ የማዕድን ግብይት ላይ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎቸ ተፈፃሚ የሚሆነው አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኃላ ይሆናል፡፡

**፴፱. የተሻሩ ሕጎች**

፩. የከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፩/፪ሺ፩ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፵. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፵፩. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሀሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



**38. Transitory Provisions**

The provisions of this proclamation shall be applied to minerals transactions other than precious minerals transactions after six months starting from the date of the coming in to force of this Proclamation.

**39. Repealed Laws**

1. The precious Mineral Transaction Proclamation No. 651/2001 is hereby repealed.
2. No law, Regulation, Directives or Customary Practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters governed by this Proclamation.

**40. Power to Issue Regulation and Directives**

The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

3. The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to sub article 1 of this Article.

**41. Effective Date**

This Proclamation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On the 15th Day of August , 2019**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**